# ዜና ቤተ ክርስቲያን



ጌታ በዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ

አዲስ አበባ ጥር ፲ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ ም

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ

www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ቤተ ክርስቲያን



ጌታ በዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ

አዲስ አበባ ጥር ፲ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ ም

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ

www.ethiopianorthodox.org

# ማ ው ጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| ፩ ርእሰ አንቀጽ | 4 |
| ፪ የቅዱስነታቸው የሰላም መልእክት | 5 |
| ፫ ከመንፈሳዊ ዓለም የተገኙ ዜናዎች | 9 |
| ፬ ግዝረት ምንድነው ጥምቀትስ ? | 16 |
| ፭ ስለሥጋዌ ምን ያውቃሉ ? | 19 |
| ፮ TIMKET (EPIPHANY) | 22 |


www.ethiopianorthodox.org

# ዜ ና ቤ ተ ክ ር ስ ቲ ያ ን

በኢትዮጵያ መንበረ ፓትርያርክ በታሪክ ፣ ድርሰትና ስብከት የስነ ጽሑፍ ማደራጃ ክፍል በተለይ ለጥምቀት በዓል የተዘጋጀ ፣

አ ዘ ጋ ጅ

ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ

ርእሰ አንቀጽ

## የጥምቀትን በዓል ስናከብር

በክርስትና ዓላም ውስጥ ከፍተኛ የታሪክ ምዕራፍ የተሰጠው አንድ ታላቅ የበዓል ቀን አለ ። ይህ ታላቅ የበዓል ቀን በመላው ክርስቲያኖች ዘንድ በታላቅ ክርስቲያናዊ ስሜት ይከበራል ። ይኸውም ክርስቲያኖች በሥጋ ከእናት ከአባታቸው ከተወለዱ በኋላ በመንፈስ ከእግዚአብሔር የተወለዱበት የጥምቀተ ክርስቶስ በዓል መታሰቢያ ዕለት ነው። በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኘ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ተዛምዶ የሚቈጥረውና የሚያስታውሰው በዚህ ዕለት ነው « ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ፣ ከመንፈስ የተወለደ ግን መንፈስ ነው » የሚል ጽሑፍ ስለአለ ክርስቲያኖች በሥጋ ከእናት ከአባታቸው ከተወለዱ በኋላ እንደገና በመንፈስ ከእግዚአብሔር ባይወለዱ ኑሮ ከሥጋዊውና ከደማዊው ፍጡር (ከእንስሳ) የተለየ ግምት ሊሰጣቸው አይችልም ነበር ከእዚህም በቀር «ከውኃና ከመንፈስ ያልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ቀርቶ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማየት አይችልም» ተብሎ ስለተጻፈ የክርስቶስን በዓለ ጥምቀት የመታሰቢያ ዕለት በምናከብርበት ጊዜ ጥምቀት የመንግሥተ ሰማያት በር መክፈቻ ቍልፍ መሆኗን እንረዳለን ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለራሱ ጥምቀት የማያስፈልገው ንጹሐ ባሕርይ ሲሆን ጥምቀትን ለእኛ ባርኮ ቀድሶ ባይሰጠን ወይም የክርስትና ጥምቀት ባይኖረን ኖሮ ምንተባለን እንጠራ ነበር ? ከዚህ በላይ ከተረዳነው ሌላ ወንጌል ስለዚህ ምን ይናገራል ? ባናምንና ባንጠመቅ ኑሮ አሕዛብ ተብለን እንጠራ ነበር « ወንጌል ያመነ የተጠመቀ ይድናል ፣ ያላመነ ያልተጠመቀ ግን አይድንም » ይላል ። በዚህ ረገድ አሕዛብ ወይም አረመኔ ከመባል ነፃ ወጥተን ክርስቲያን የተሰኘውን ታላቅ ስም የተቀበልንበትን መንፈሳዊ ነፃነት ስናስብ ክርስቶስ ለእኛ አርአያ ለመሆን በዮርዳኖስ ውኃ የተጠመቀበትን የመታሰቢያ ዕለት ምክንያት በማድረግ በእየእንዳንዳችን ልቡና ውስጥ ለጥምቀት የምንሰጠው የክብር ሥፍራ እጅግ በጣም ከፍ ያለ ነው ።

በኢትዮጵያውያን አባቶች ዘንድ «ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ» የሚል ጥንታዊ አነጋገር አለ ። ይህም ሴቶችም ቢሆኑ ወንዶች የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ለበዓለ ጥምቀት የሚሰጡትን ከፍተኛ ክብር ያስረዳል ። በአሁኑ ጊዜ ግን ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ በሚለው ፈንታ ለጥምቀት ያልሆነ ወጭ የሚለው ዘይቤ ተተክቶ በዚህ ዘመን አስተርእዮ ተብሎ በሚጠራው ክፍለ ጊዜ የብዙዎች የጥሆች ኢኮኖሚ ዝ ቅ ብ ሎ ይ ታ ያ ል ። እ ን ደ ዚ ህ የሚያደርጉ ሁሉ እጅግ በጣም ተሳስተዋል ፣ አስተሳሰባቸውም ከክርስቲያናዊ አስተሳሰብ ውጭ ነው ። መንፈሳዊ በዓል የችግር ምክንያት አይደለም የጥምቀትን በዓል ስናከብር በመጠኑ ሥጋዊ ደስታ ሊኖረን የሚገባ ቢሆንም በዮርዳኖስ ተቀብር የነበረው የበደል ደብዳቤአችን በክርስቶስ ጥምቀት የተፋቀ ልን መሆኑንና መንፈሳዊ ነፃነት የተቀበልን መሆናችንን ማሰብ እንጂ ፈጽመን ለሥጋዊ ፍላጐታችን ብቻ ምርኮኞች መሆን አይገባንም ።

ከዚህም ጋር በበዓለ ጥምቀት ጊዜ በምናደርገው የሀገር ባህል ጨዋታ መንፈሳዊውንና ብሔራዊውን ደስታ በኅብረትና በፍቅር በመከፈል ፈንታ በአሥራ አራቱ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች በመከፋፈልና የወገን ልዩነት በማድረግ ከአንድ አፈር የተፈጠርን አንድ ሃይማኖትና አንድ ኅብረ መልክ ያለን ወንድማማቾች ስንሆን ርስበርሳችን ፀብ ክርክር በማድረግ በሌሎች ዓላማት የተመሰገነውን ቅድስናችንና ንጹሕ የሆነውን ታሪካችንን ስናጐድፍ እንታያለን ። ይህ መሠረተ ቢስ አድራጎት የጥንታውያን ኢትዮጵያውያን ዜጎች ልማድ ባለመሆኑ በአበው ዘንድ ሊያስነቅፈንና ሊያስወቅሰን ይችላል ስለዚህ ከአበቶች የሚወረሰው ርስታቸውና ሀብታቸው ብቻ ሳይሆን በጎ ምግባራቸውና ባህላቸውም ጭምር ስለሆነ ኢኮኖሚአችንን በመጠበቅ ይህን ታላቅና መንፈሳዊ የጥምቀትን በዓል በኅብረትና በፍቅር ማክበር ይገባናል ።



www.ethiopianorthodox.org

# ሰላም የምትገኘው ከእግዚአብሔር ነው "

ቴዎፍሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ልደት ምክንያት በማድረግ ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ፳፬ ዓ/ም ሐሙስ ማታ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥንና ሬዲዮ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ዓቢይ ርእስ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የሰላም መልእክት ለሕዝበ ክርስቲያን አስተላልፈዋል ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

« እስመ ሕፃን ተወልደ ለነ ፤ ወልድ ተውህበ ለነ ፤ ወቅድመት ከነ ዲበ መትከፍቱ፤ወይሰመይ ስሙ ዐቢየ ምክር ፤ አበ ዓለም ወመላከ ሰላም ፤ እስመ ውእቱ ያመጽእ ሰላመ ለመላእክት ወሕይወት ዚአሁ ፤ ወዐበይ ቅድሜሁ ፤ ወአልበ ማሕለቅት ለሰላሙ ፤ ዲበ መንበረ ዳዊት ትጸንዕ መንግሥቱ »

ሕፃን ተወለደልን ፤ ወልድ ለእኛ ቤዛ ሆኖ ተሰጠልን ፤ሥልጣኑ የባሕርዩ ነው ፤ ስሙም ብርቱ ፤ መካር ፤ የሰላም መሪ ይባላል ፤ እሱ ለመሪዎች ሰላም ን ያሰጣል ፤ ሕይወቅ የርሱ ነው ፤ አምላክነት ገንዘቡ ነው፤ ለሰላሙ ፍጻሜ የለውም ፤ በዳዊቅ ዙፋን ላይ መንግሥቱ ትጸናለች » ፤ ትንቢተ ኢሳ ም፡ ፱፡ ቍ፡ ፮—፯ ።

የሰው ልጅ በምድር ላይ መባዛት ከጀመረበት ጊዜ ወዲህ በልዩ ልዩ ቤተ ሰብ መካከል ብዙ ሕፃና ት ተወልደዋል ፤ ግን እንደዚህ ዓይነት ትምክሕት እንዲሁም ተስፋና ክብር የተሞላበት ቃል የተነገረለት ሕፃን አልተገኘም ። አንዳንድ ታላላቅ ሰዎች ከመወለዳቸው አስቀድሞ ለወላጆቻቸው የብሥራት ቃል ተነግሮአል ። ግን ይወለድልሃል ፤ ይወለድላችኋል የሚል በአጭሩ የተወሰነ ቃል እንጂ ተወለደልን ተሰጠልን የሚል አጠቃላይ ቃል አይገኝለትም። ስለ ክብሩም የራሱን ብቻ የሚያመለክት እንጂ የዓለም ሁሉ ሥልጣን ፤ የዓለም ሁሉ ሰላም ይልቁንም አምላክነቅ ቀዳማዊነት የተነገረለቅ የለም ።

ይህ ሁሉ የተነገረለት ፤ በአምላክነቱ የሚታደገን ከመሆኑም በላይ ሰው ሆኖ ለተዛመደን ፤ ሕይወቱን ሰላሙን ለሕያለን ፤ እኛን መሕሉ በበረቅ ለተወለደው እንኳን ለእግዚአብሔር ልጅነቱ፤ ለዳዊቅ ልጅነቱም ይበቃል ተብሎ በማይገመት ቦታ ለተገለጠው ፤ ሰው ለሆነው አምላክ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው ። ሕፃኑ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአባት ያለ እናት ፤



ቅዱስነታቸው የሰላም መልእክት ባስተላለፉበት ጊዜ

ከእናት ያለ አባት ለመወለድ የተቻለው ስለሆነ « ብሁተ ልደቅ » በልደት ሥልጣን ያለው መሆኑን አሳይቶአል ። እንዲሁም ከአባትና ከእናት በሥጋ በደም በሚወለዱት ልደት ላይ የመንፈስ ልደትን እንዲያገኙ ለተቀበሉት ሁሉ ሥልጣን ሰጥቶአል ።

የቀደሙ ነገሥታት ነቢያት ሀብተ ፀጋን ከእሱ ታደሉ ፤ እሱ ግን ለተቀበሉት ሁሉ የእግዚአ

፯

www.ethiopianorthodox.org

ብሔር ልጆች እንዲሆኑ ሥልጣን ሰጠ ፤ በዚህም ሥልጣን ገንዘቡ መሆኑን ገለጠ ፤ ቃል ሥጋ ሆነ ፤ በእኛም አደረ ፤ ከአባቱ ጋር እኩል ትክክል የሆነ ክብሩንም አየን ፤ ከምላቱም እኛ ሁላችን በፀጋ ላይ ፀጋን ተቀበልን ።

በቀደሙ ሰዎች ዘመን ገጸ እምላክን ለማየት ካለመቻሉም በላይ ገጸ መልአክ ማየቱም የሞት ፍርሐት ያሳድር ነበር ። በኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ግን ገጸ መልአክ ገጸ አምላክም ለመታየት ተቻለ ።

የተወለደውም የሕይወት ባለቤት ስለሆነ ላዩት ሁሉ የተሰማው ቃል «እያዧችሁ አትፍሩ ለእናንተና ለዓለም ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁ ። እነሆ ዛሬ በዳዊት አገር መድኅን ተወልዶላችኋል » የሚል ነበር ።

በቀድሞው ዘመን የተወለዱት ጀግኖች በታዳጊነታቸው ድካም ነበረበት ፤ በቦታም የተወሰነ ነበር ። የእሱ ታዳጊነት ግን ድካም የማይቀላቀልበት በታ የማይወሰንበት በሁሉ ለሁሉ የሚደርስ ስለሆነ ሰውና መላእክት አንድ ሆነው የልደቱን ደስታ ለመካፈል ቻሉ ።

የዓለም ሕዝቦች ሰላምን ለማግኘትና ለማስገኘት ይጥራሉ ። ግን ሰላም የምትገኘው ከእግዚአብሔር ነውና እንዲህ ያለው ጥረት በሃይማኖት ሊደገፍ ይገባል ። ስለዚህ ነው የሰላም ባለቤት ፤ የዓለም ጌታ በተወለደበት ጊዜ ሰላምን ለዓለም ያመጣ ፤ በጨለማ መካከል ማለት በመንፈቀ ሌሊት በተወለደበት ዙሪያ ፍጹም ብርሃን ተገለጠ « አይዟችሁ አትፍሩ » የሚል አጽናኝ ቃልም ተሰማ ። እንዲሁም « በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና ተገባው ፤ በምድርም ሰላም ሆነ ለሰው ልጆች እርቅ ተጀመረ» የሚል መዝሙር ተዘመረ ።

የሰው ልጅ አምላክ ለመሆን ከቃጣበትና የአምላኩን ትእዛዝ ከተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ በሞት ፍርሃት ተውጦ ፀጥታና ሰላም አጥቶ ይኖር ነበር ። ሰው ለሞት ፍርሃት ከመገዛት ነፃ ወጥቶ ፍጹም ዕረፍት አግኝቶ እንዲኖር ሰው የሆነው አምላክ በአገልጋይ መልክ ተገለጠ ፤ በድኃ ቤት እንኳ ሳይሆን በእንስሳት መካከል በበረት ተወለደ ይህንን ያደረገበት ምክሩን ማንም ሳያውቀው ረቂቅ ስለሆነ ነቢዩ «ይሰመይ ስሙ ዓቢየ ምክር ፣ አበ ዓለም ወመልአከ ሰላም ስሙ ብርቱ መካር የዓለም አባት የሰላም አለቃ ይባላል» ብሎ ተናገረ ።

ዛሬ የዓለም አባት የሰላም አለቃ ሰው የሆነው አምላክ የተወለደበትን ቀን በፍጹም ደስታ እናከብረዋለን ። ግን የሰው ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰበከለትን ሰላም ትቶ ፤ ይህ ዓለም በወንድማማችነት ሊኖርበት የተፈጠረለት መሆኑን ዘንግቶ ርስ በርስ በሚያደርገው ደም መፋሰስ በሰው ልጆች መካከል ፀብ ገኖ ፤ ሰላም መንምና ስንመለከት ታላቅ ኃዘን ይሰማናል ። ዘመናችን የሰው ልጅ በሥጋዊ ዕውቀት ጠልቆ ፤ በጥበብ መጥቆ የሔደበት ፤ ምቾት የበዛበት ሆኖ የሚታየውን ያህል በዚያው አንፃር ይህን ሁሉ የሚያጠፋ ሥራ ሲሠራ መታየቱ እጅግ ያሳዝናል ። እዚህ ላይ በጦር መሣሪያ ብልጫ ለማግኘት የሚደረገውን እሽቅድምድምና በየቦታው ያለውን ጦርነት ሳናስታውሰው አናልፍም ።

ስለዚህ ኃያላንም ድኩማንም በአንድ ልብ ፤ በአንድ ኃይል ሰላምን ጠብቀው ሊኖሩና ከዕውቀት የተገኘውን ፍሬ ለሰው ዘር ማጥፊያ በማድረግ ፋንታ ለሰው ልጅ ሕይወት መደገፊያ ሊያደርጉት ይገባል ። እግዚአብሔር ሰው ሆኖ የፈጸመውን የሰላም ሥራ ከንቱ አድርጐ መመልከት ጉዳትን ያመጣል ፤ ሁሉም በሃይማኖትና በፍቅር አንድ ሆኖ ዓይኑን ወደ እግዚአብሔር ቢመልስ ትክክለኛ ፍርድ ይገኛል ፤ ሰላም ይሰፋል ፤ የጥል ግድግዳ ይፈርሳል ፤ የቤተ ክርስቲያን ምክርና ትምህርት ይህ ነው ።

ከሰላሙ ባለቤት ፤ ከሰላሙ ጌታ ፤ ከሰላሙ ንጉሥ ለቀረቡትም በሩቅ ላሉትም ሰላም እንዲሆንላቸው እንጸልያለን ።

## የቅዱስነታቸው ጸሎት

እኛን ለማዳን ሰው ሆነህ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለድከው ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ፤ ለአንተ ለቸር አባትህ ለመንፈስ ቅዱስም በሰማይ ምስጋና ይሁን ፤ በምድርም ሰላምና እርቅ ለሰው ልጆች ይሁን ፤ አቤቱ ፈጣሪያችን ሆይ ፤ አንተን በመውለዷ ፤ የአንተ እናት በመሆኗ የወገናችን መመኪያ በሆነችው በእናትህ በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ተማጽነን ሀገራችን ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ፤ ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን በቸርነትህ ፤ በታዳጊነትህ እንድትጠብቃቸው ለመላው ዓለም ሰላምን ፍቅርን ፤ ትክክለኛ ፍትሕን እንድትሰጥልን እንለምንሃለን አሜን ።

## ከመንፈሳዊ ዓለም የተገኙ ዜናዎች

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ታኅሣሥ ፴ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ፡ ም እሑድ በአዲስ አበባ ወልደ ነጐድጓድ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው በማስቀደስ የአጥቢያው ምእመናን በመተባበር ያሠሩትን የቀሳውስት ማደሪያ ቤትና



www.ethiopianorthodox.org

የቤተ ክርስቲያኑን ዙሪያ የብረት አጥር እንዲሁም የጸሎተ ፍትሐት ማድረጊያ ሥፍራ ከጐበኙ በኋላ ከፍተኛ መንፈሳዊ አገልግሎት ለአበረከቱት ምእመናን ደረገላቸው ታላላቅ ሰዎች ተገኝተዋል ።

ከቤተ ክርስቲያኑ ጽ/ ቤት በወጣው ፕሮግራም መሠረት ከጥዋቱ በ፫ ሰዓት የጸሎተ ቅዳ



ቅዱስነታቸው የቀሳውስቱን ማደሪያ ቤት በጐበኙበት ጊዜ

ሴው ስነ ሥርዓቱ እንደተፈጸመ ክቡር ንቡረ ዕድ ኤርምያስ ከበደ ለምእመናን በሰጡት ምክር የቤተ ክርስቲያን ሰዎችና ምእመናን መንፈሳዊ ግንኙነት በግ ድረግ አበው በአጥንታቸውና በደማቸው የፀነቧትን ቤተ ክር ስቲያንን መርዳት ተገቢ መሆ ኑን አስረድተዋል ። ንቡረ ዕዱ

የመልካም አገልግሎታቸው መገ ለጫ የሆነ የምስክር ወረቀት ሰጥተዋል ። በጉብኝቱና የምስ ክር ወረቀቱን በመሰጠቱ ስነ ሥር ዓት ላይ ክቡር ንቡረ ዕድ ኤር ምያስ ከበደ የጠቅላይ ቤተ ክህ ነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የአ ድባራት አለቆች እንዲሁም የአ ጥቢያው ሽማግሌዎችና ጥሪ የተ



ምክራቸውን በመቀጠል ቤተ ክርስቲያን ስትባል የመላው ክርስቲያኖች እንጅ የካህናት ብቻ አለመሆኗን ከገለጹ በኋላ በአሸዋ ላይ የተመሠረተ ቤት ዋጋ እንደሌለው ሁሉ ምግባርና ሃይማኖት የሌለው ቅውልድም ለሀገርም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን ሊጠቅም ስለማይችል ወላጆች ልጆቻቸውን በመልካም ክርስቲያናዊ አስተዳደግ ማሳደግና ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ማቅ ረብ ክርስቲያናዊ ግዴታቸው መሆኑን ገልጸዋል ። ከዚያም የጉብኝቱ ስነ ሥርዓት ተጀምሮ ቅዱስነታቸው የቀሳውስቱን ማደ ሪያ ቤትና የቤተ ክርስቲያኑን ዙሪያ የብረት አጥር እንዲሁም የጸሎተ ፍትሐት ማድረጊያ ውን ሥፍራና በተሟላ ዝግጅት በዘመናዊ መልክ የተሠሩትን የንዋየ ቅድሳትና የአልባሳት ማስቀመጫ ቁምሣጥኖች አንድ በአንድ ተመልክተዋል ።

ከጥዋቱ በ፩ ሰዓት ጉብኝቱ ተፈጽሞ ቅዱስነታቸው ለምስ ክር ወረቀት መስጫ በተዘጋ ጀው ሥፍራ እንደተገኙ የቤተ ክርስቲያኑ ተጠባባቂ አስተዳዳሪ ቄስ ዘውዴ ወልደ ማርያም በዮ ሐንስ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ በሌ ላው ምእመናን ይህ ዓይነቱን መንፈሳዊ ፍሬ ለማፍራት የቻ ሉት በቅዱስነታቸው ዘመናዊ አመራር መሆኑን በመጥቀስ የዮ ሐንስ ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ ምእመናን ትንሽ ትልቅ ሽማ ግሌ ሕፃን ሳይባል ከካህናቱ ጋር በመተባበር በገንዘባቸውም ሆነ በጉልበታቸው ባደረጉት

የተቀደሰ ጥረት ይህን የመሰ ለው መንፈሳዊ ርምጃ ሊደ ረግ የቻለ መሆኑን በመግ ለጽ የቀሳውስቱ ማደሪያ ቤትና የሌላው ዝግጅት ጠቅላላ ወጭ ከ፲፱ ሺህ ብር በላይ መሆኑን አስረድተዋል ። ከዚህ በኋላ ቅዱ ስነታቸው የሚከተለውን ቃለ በረ ከት ሰጥተዋል ።

## የቅዱስነታቸው ቃለ በረከት

«እኛ ኢትዮጵያውያን አንድ ዘውድ አንድ ሃይማኖት ያለን ሕዝቦች ነን እናንተም ይህን ተረ ድታችሁ የሌላውን ስትከተሉ ጥርስና ጥርስ ከንፈርና ከንፈር ቢተባበር ያምር» እንደሚባለው ሁሉ ተግባራችሁ የተቀደሰ ርምጃ ማሳየታችሁ የሚያስመ ሰግን ነው ። እኛን ደስ እንዳ ለን እግዚአብሔርንም ደስ ይለ ዋል ። ቤተ ክርስቲያን ምድራ ዊቅ መንግሥቅ ስለሆነች የመ ንግሥተ ሰማያት ምሳሌ በሆን ችው በቤተ ክርስቲያን ምእመ ናን በኅብረት መሰብሰብና መንፈ ሳዊ ሥራ መሥራት ይገባቸዋል።

ይህ ያዘጋጀሁት መንፈሳዊ ዝግጅት ለአገልጋዮቻችሁ ካህና ትና እናት አባት ለሌላቸው የሟ ች ልጆች ረዳቅ የሆንችውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የሚ ረዳ ስለሆነ ክርስቲያናዊ ግዳጃች ሁን ፈጽማችኋል ። የሰው ልጆች ከተባበሩ የሚቸግር ነገር የለም ። ብዙ ሰው እግዚአብሔር ነው የሚለው አነጋገር ስለዚህ ነው።

በጐች እረኛቸውን ካወቁ እረኛቸውም በጐቹን በሚገባ ከጠበቀ ችግር የለም ። አስፈ



www.ethiopianorthodox.org

ላጊ ከሆነው በስተቀር በሃይማ ኖታችን ረገድ የእኛን ትተን የሌላውን መከተል አይገባንም ፤

መጽሐፍ ቅዱስ በልዩ ልዩ ቋንቋ ቢተረጐምም በሃይማኖቅ ረገድ ቃሉ አንድ ነው ፤ ስለዚህ ሃይማኖታችሁን መለወጥ አይገ ባችሁም። መለያየት ድካም ነው። መተባበር ግን ኃይል ነው ይህን ከፍተኛ ሥራ ለመሥራት የቻላ ችሁት በመተባበራችሁ ነው ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሌ ሎች አርአያ ሆንኳቸው ብሎ እንዳስተማረው ሁሉ የዮሐንስ አጥቢያ ምእመናን ለሌሎች አር አያ በመሆናችሁ ትመሰገናላ ችሁ። ቀዳሚሁ ቃል የተባለውን ረቂቅ ምሥጢር የተረጐመውና ያስተማረው ወንጌላዊው ዮሐ ንስ ወልደ ነጐድጓድ በመሆኑ እናንተም የርሱን አርአያ ተከ ትላችሁ ከፍተኛ መንፈሳዊ ቍም ነገር በመፈጸማችሁና ለሌሎች መልካም አርአያ በመሆናችሁ ትመሰገናላችሁ ። ሆኖም ይፀ የተመለከትነው ሁሉ የክርስቲያ ናዊ ግዳጃችሁ አበባ ስለሆነ ወደ ፊት ፍሬውን እንጠብቅባችኋለን በማለት ቃለ በረከት ከሰጡ በኋላ ከፍተኛ አገልግሎት ላበረከቱት ምእመናን የምስክር ወረቀት ሰጥ ተውና ከምእመናኑ ጋር የመታ ሰቢያ ፎቶግራፍ ተነሥተው ለአ ምስቅ ሩብ ጉዳይ የጠቅላላው ስነ ሥርዓት ፍጻሜ ሆኗል ። በዚሁ ሰዓት ፫ ሊቃውንት ለቅ ዱስነታቸው የመወድስ ቅኔዎች አበርክተዋል ።

## ፓትርያርኩ የፈረንሳይን ተወላጆች አነጋገሩ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎ ፍሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓ ትርያርክ ዘኢትዮጵያ ሐሙስ ታኅሣሥ ፳፯ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ ም ከቀትር በኋላ በ፲፱ ሰዓት ላይ በግል ጉብኝት የሰነበቱ ፯ የፈ ረንሣይ ተወላጆች በመንበረ ፓትርያርክ ተቀብለው አነጋገሩ።

ቅዱስነታቸው እንግዶቹን ተ ቀብለው ያነጋገሩት በእንግዶቹ መሪ በሪቨሬንድ ርኩዊቅ አማካይነት ነው ።

ሬቨሬንድ ሺሬ የካቶሊክ እምነ ት ተከታይ ሲሆኑ እሳቸውም ለአርባ ዓመታት ያህል በዓል ፈቃዳቸው አብያተ ክርስቲያን አንድ እንዲሆኑ በመጣር የቆዩና የሚሠሩ ናቸው ። ከዚህም ሌላ የይሁዳ እምነት ከክርስቲያን ሃይ ማኖት ጋር ያለው ግንኙነት ወ ይም ልዩነት እንዴት እንደሆነ ያጠኑ ከመሆናቸውም ሌላ ስለ ዚህ ጉዳይ የተዘጋጀ ዳያሎግ እንዳላቸው ለብፁዕ ወቅዱስ ነታቸው አስረድተዋል በተጨ ማሪም ወደ ሀገራቸው እንደተ መለሱ ዳያሎጉን ለብፁዕ ወቅ ዱስ ፓትረያርኩ እንደሚልኩላ ቸው ገልጸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስአቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን አቋምና ይዞታ እንዲሁም ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር ስላለ ላት መቀራረብና ይዞታ ለእንግ ዶች አስረድተዋል ።

ኢትዮጵያን » መጐብኘታቸውን ገልጸው «የሰሎሞንን ሀገር ኢየ ሩሳሌምን» ከጐበኙ በኋላ በቀ ጥታ ወደ መኖሪያ ሀገራቸው



ቅዱስነታቸው የፈረንሳይን ተወላጆች ሲያነጋግሩ

በመጨረሻም ብፁዕ ወቅዱ ስነታቸው ጸሎተ ቡራኬ አድር ገው እንግዶቹን አሰናብተዋል።

እንግዶቹም «የሳባን ሀገር ወደ ፓሪስ እንደሚመለሱ አስ ታውቀዋል ። እነሱም ሁለት ሴ ቶች ና አምስት ወንዶች ሲሆኑ ሁሉም የካቶሊክ እምነት ተከታ ዮች መሆናቸው ታውቋል ።

## የአፍሪካ ወጣቶች ጉባኤ ተፈጸመ

ከታኅሣሥ 10—22 1964 ዓ. ም በናይጀሪያ በተደረገው በመላው አፍሪቃ ተማሪ ዎችና ወጣቶች ጉባኤ ከ28 የአፍሪካ አገሮች የተው ጣጡ 138 አባሎችና ከየክፍላተ ዓለሙ በተመልካችነት 40 ተመ ልካቾች ተገኝተዋል ።

ጉባኤው በ12 ቀናት ውስጥ በልዩ ልዩ ርእሶች ላይ ከፍተኛ



www.ethiopianorthodox.org

ውይይት ሲያደርግ ሰንብቷል። በመጠኑ ለመጥቀስ ያህልም ፤

በአፍሪካ የሚሰጠው ቅምህርቅ በቅኝ ገዥዎች የሚመራ ስለሆነ አፍሪካውያን የነበራቸውን ባህልና ነፃ አስተሳሰብ ገፎ የውጭ አስተሳሰብ ተገዥ አድርጓል።

ይህትምህርት ነፃ የአስተሳሰብ ዕድል አይሰጥም። ስለዚህ በአፍሪካ ምድር ውስጥ ሊሰጥ የሚገባው የቅምህርት ዓይነት ከሕዝቡ ፍላጎት ባህል እምነትና ከአገሩ የተፈጥሮ ሀብት የመነጨ ቢሆን ነፃ ኅብረተ ሰብእ መመሥረት ይቻላል። እንዲያውም የሚቻል ቢሆን አፍሪካዊ ቋንቋ ፈልጎ የመማሪያ ቋንቋ ማድረግም አንዱ ርምጃ ነው። ይህ ሲባል የአፍሪካ አገሮች ሥነ ጽሑፍ በእንግሊዘኛና በፈረንግ ይኛ ቋንቋ መሆኑን በመዘንጋት አይደለም።

ይህ የአሁኑ ትምህርቅ ውድድርን የማይሹ ጥቂት ሊቃውንቅ ለመፈጠርና ሠራተኛውን ከሥራው የማያገናኘው መሆኑ ግልጽ ነው። ስለዚህ የአፍሪካ አገሮች ለትምህርት የሚያጠፉት ወሰን የሌለው ገንዘብ ከጥቅም ላይ እንዲውል ከፈለጉ የትምህርቅ አሰጣጥ ዘዴያቸውን አሁኑኑ ቢለውጡ ይሻላል።

ዛሬ በአፍሪካ ውስጥ ነፃነታቸውን ያላገኙ ጥቂቶች አገሮች መኖራቸው አፍሪካን አስቸግሯታል።

ይህ ነፃ የወጡቅን የአፍሪካ አገሮች የመተባበር ድካም ያሳያል በእያንዳንዳቸው የአፍሪካ አህጉር ላይ የባዕድ ተፅዒኖ ባይኖርኖሮ በነፃ ማውጣት ላይ የሰማይና የምድርን ያህል ርቀት ያለው ሐሳብ ባልተፈጠረም ነበር። ይህ ዓይነቱ የሐሳብ መከፋፈል ያለው በመንግሥታት ላይ ብቻ ሳይሆን በአብያተ ክርስቲያናቅም መካከል መታየት ጀምርአል። ይህም አብዛኛዎቅ የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ቅምህርታቸውና ሥራቸው ያው በቅኝ አገዛዝ ዘመን እንደነበረው አለመለወጡን መረዳት ይቻላል። ስለዚህ ወንጌሉ ነፃነትን የሚያበሥር ሆኖ ሳለ ነፃ ወዳልወጡት የአፍሪካ አገሮች ጉዳይ ሲዞር እነሱም ፊታቸውን ያዞራሉ።

ስለዚህ አብያተ ክርስቲያናት በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት ነፃ ስላልወጡትና በጭቆና አገዛዝ ስር ስለሚሰቃዩት ሰዎች እውነተኛውን ቅገል ማድረግ ይገባቸዋል። ያለዚያ ተልእኮአቸውን በሚገባ አልፈጸሙምና በሁለቱም ቦታዎች ያስጠይቃቸዋል።

እንዲሁም አፍሪካውያን ሊኖራቸው የሚገባ ባህል የቱኛው ነው ፤ በሚለው ዐቢይ ርእስ ላይ ክረር ያለ ውይይት ተደርጎበታል። እንዲሁም በየአገሩ በጥገኝነት የሚገኙት ስደተኞች ጉዳይ ተነሥቶ ብዙ መሪጃዎች ከተሰሙ በኋላ አፍሪካውያን ስደተኞች በአፍሪካ አገር ሲኖሩ ስደተኞች ተብለው ባይጠሩስ ? ብቻቸውንስ ተገልለው ከሚኖሩ በስደት በሚኖሩበት አገር ካለው ኅብረተ ሰብዕ



በሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ስም የጉባኤው ተካፋዮች ከነበሩት በከፊል ።

ጋር ቢቀላቀሉስ ? ሥራ የማግኘት ዕድልስ ቢኖራቸው ምናለ ? በሚሉት አቅጣጫዎች ብዙ ውይይት ተደርጓል።

በአጠቃላይ አስተያየት ጉባኤው ለአፍሪካ ወጣቶች የመጀመሪያ በር ከፋች ሆኗል። ይህ ዓይነቱ ጉባኤ በየጊዜው እንዲደረግ ስምምነቅ ተደርጓል። በዚህ ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያም በሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ስም መልእክተኞችን በመላክ ተካፋይ ሆናለች።


www.ethiopianorthodox.org

# ግዝረት ምንድን ነው? ጥምቀትስ ?

ረታዒ ቤተሰብ
የግል ቤተ መጻሕፍት

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአባታችን ለአዳም የሰጠውን ተስፋ ለመፈጸም ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ሕገ ኦሪትን ለመፈጸም በተወለደ በስምንት ቀኑ ጥር ፮ ቀን ቤተ ግዝረት ገብቷል። ይህም ሕገ ግዝረት አስቀድሞ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው አምላካዊ የቃል ኪዳን ሕግ ነው፤ቃሉም እንዲህ ይላል፤ « እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው አንተ ደግሞ ቃል ኪዳኔን ትጠብቃለህ በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ በዘርህ መካከል የምትጠብቁት ቃልኪዳኔ ይህ ነው ከአንተ ወንድ የሆነ ሁሉ ይገረዝ የቁልፈታችሁንም ሥጋ ትገረዛላችሁ በኔና በናንተ መካከል ላለውም ቃል ኪዳን ምልክት ይሆናል የስምንት ቀን ወንድ ልጅ ይገረዝ በቤት የተወለደ ወይም ከዘራቸው ያይደለ ፤ በብርም የተገዛ ወንድ ሁሉ በትውልዳችሁ ይገረዝ ፈጽሞ ቃልኪዳኔም በሥጋችሁ የዘለዓለም ቃል ኪዳን ይሆናል የቁልፈቱን ሥጋ ያልተገረዘ ቈላፍ ሰው ሁሉ ያች ነፍስ ከወገንዋ ተለይታ ትጥፋ ቃል ኪዳኔን አፍርሳለችና ይላል ፤ ዘፍጥረትም ፲፯፣ ቍ ፱—፲፬ አብርሃም ይህን ቃል ኪዳን በተቀበለበት ቀን ልጁ እስማኤልና ቤተሰቦቹ በሙሉ በዚሁ ቀን ከርሱ ጋር ተገርዘዋል ።

፬ተኛም አሪት ዘሌዋውያንም፡ ፲፪፣ ቍ፣፩—፬ እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ለእሥራኤል ልጆች ሁሉ እንዲህ ብለህ ንገራቸው ሴት ብታረግዝ ወንድ ልጅም ብትወልድ ፯ ቀን ያህል የረከሰች ናት እንደሕመሟ መርገም ወራት ትረከሳለች በ፰ኛውም ቀን ልጁ ከሥጋው ሸለፈት ይገረዝ ብሎታል ። በዚህ ሕግና ሥርዓት መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ በ፰ ቀን ወደ ቤተ ግዝረት ገብቷል ። ቤተ ግዝረት ገባ ስላልንም ሕገ ኦሪትን ለመፈጸም ያህል ነው እንጂ የባሕርይ አምላክ ሰውነቱ በሰው እጅ የሚገሬዝ ሆኖ አይደለም ። እመቤታችን ንጽሕት ድንግል ማርያምም እንደሌሎች ሴቶች ርስሐት ኖሮባቅ በ፯ ቀን የምትነፃ ሁና አይደለም ፤ ነገር ግን ምቀኞች አይሁድ ሕገ ኦሪቱን አፈረሰ እንዳይሉት ምክንያት ለማጥፋት ነው ።

ስለዚህ ከላይ እንደገለጽነው በቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትም እንደተረዳነው ጥር ፮ ቀን ግ ክሰኞ ቤተ ግዝረት በገባ ጊዜ እመቤታችን ዮሴፍን ሂድ ብልህ አዋቂ የሆነ ገዛሪ ፈልገህ አምጣልኝ እንደሙሴ ሕግ ልጄን ይገርዘው ዘንድ አለችውና ዮሴፍ ሂዶ ብልሁን ገዛሪ አመጣው ገዛሪውም ሕፃኑን ያዙልኝ እገርዘው ዘንድ እችላለሁና እንዳይቈስል ብሎ ተናገረ ሊሆን በቀራንዮ በመስቀል ላይ ቀኝ ጐኔን በወጉኝ ጊዜ ከሚፈሰውና ወደ ምድር ከሚወርደው ደሜ በስተቀር



ሕፃን ተወልዶልን ወንድ ልጅም ተሰጠን ኢሳ ፱ ፮—፰

ወዲያውም ምላጮቹን ይዞ ቀረበ ሕፃኑም ጠቢብ ሆይ ቅዳር ዘኝ ዘንድ ቻሎታህንና ጥበብህን እስኪ አይልሃለው የአዳምና የዓለም ሁሉ መድኃኒት ደሜ በዚህ ዓለም አይፈስም አለው ፤ በዚህ ጊዜ ብልሁ ገዛሪ የባሕርይ አምላክ መሆኑን ተረድቶ ምላጮቹን ሰበሰበና ለሕፃኑ ከእግሩ በታች ሰ



www.ethiopianorthodox.org

ገዶ ምላጮቹም በዚያ ጊዜ እን
ደ ሰምዕ ቀለጡ ፤ እንደ ውሃም
ሆኑ ፤ እመቤታችንንም ይህ
ልጅሽ ከአዳም ዘር አይደለም።
አምላክ የአምላክ ልጅ ነው ።
እንጂ አላቅ ።

የሰው እጅ ሳይነካው በመለ
ኮታዊ ጥበቡ ግዝረቱ ተፈጽሟል
ስሙም በማሕፀን ሳይፀነስ መል
አኩ ቅዱስ ገብርኤል እንዳወጣ
ለት ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ ።
ሉቃስ ም፣ ፪ ቍ፣ ፳፩ ምሥጢረ
ልደቱ የማይታወቅ ረቂቅ እንደ
ሆነ ምሥጢረ ግዝረቱም እንዲ
ሁ ከሰው ሕሊና የተሰወረና የረ
ቀቀ ነው ።

በዚህ አኳኋን ምሥጢረ ግዝ
ረቱ ተፈጽሞ በግዕዝ ሕፃናት
ማለቅ እንደ ሕፃናት ልማድና
ሥርዓት ለእናቱ እየታዘዘና ጥቂ
ት በጥቂት እያለ ካደገ በኋላ
በ፴፩ዓ. ም. በተወለደ በ፴ ዘመን
ጥር ፲፩ ቀን በዕደ ዮሐንስ በፈ
ለገ ዮርዳኖስ ተጠመቀ ። ይህም
ከሆነና ጌታችን ለኛ ሲል ከተጠ
መቀ እስከ ዛሬ ድረስ ዘመኑ
፲፱፻፸፪ ዓመቱ ነው ። ዮሐንስ
ጌታችን መንፈቅ ቀድሞ በኢየ
ሩሳሌም አካባቢና በይሁዳ አው
ራጃዎች በዮርዳኖስ ዙሪያና በም
ድረ በዳም ሁሉ ያሉትን ሰዎች
(ነስሑ ወእመኑ እስመ ቀርበት
መንግሥተ ሰማያት) መንግሥተ
ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ
እመኑ ተጠመቁ እያለ በማስተ
ማሩ ሕዝቡን የንስሓ ጥምቀት
ያጠምቃቸው ነበር ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየ
ሱስ ክርስቶስ ግን እኛን ኃጢአ
ተኞችን ከኃጢአት ቁራኝነት
ለማስለቀቅና በጸጋ ልጆቹ እንድ
ንሆን ለማድረግ ነው እንጂ
እርሱ ንጹሐ ባሕርይ አምላክ
ሲሆን ኃጢአት ኖሮበት እንደኃ
ጢአተኞች ሰዎች የንስሓ ጥም
ቀት የሚያስፈልገው ሆኖ አይደ
ለም ። ዮሐንስ ስለእርሱ ሲመሰ
ክር ሕዝቡን እንዲህ ይላቸው
ነበር ።

«እኔ በውሀ አጠምቃችኋለሁ
ነገር ግን የጫማውን ጠፍር መፍ
ታት ከማይገባኝከኔ ይልቅ የሚ
በረታ ይመጣል ርሱ በመንፈስ
ቅዱስ ያጠምቃችኋል መንሹ
በእጁ ነው እውድማውንም ፈጽ
ሞ ያጠራል ስንዴውንም በጐ
ተራው ይከታል ገለባውን ግን
በማይጠፋ እሳት ያቃጥላል ብሏ
ቸዋል ፤ ሉቃስ ም ፣ ፫ ፣ ቍ
፲፯—፲፰ ይህ የነቢዩ አነጋገርም
የሚአስረዳን የሚከተሉትን ብዙ
ዎች ሐተታዎች በውስጡ ያዘለ
ምሥጢራዊ አነጋገር መሆኑን
ነው ከኔ የሚበረታ ይመጣል
በማለቱ የባሕርይ አምላክነቱን
እንደ መሰከረለት እንረዳለን ፤
መንሹ በእጁ ነው እውድማው
ንም ፈጽሞ ያጣራል በሚል
ውም አምላካዊ ቃሉ መንሹ በአ
ውድማ ውስጥ ፍሬውን ከገለባ
ለይቶ እንደሚአጣራ ጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስም ወደፊት
ፍርድ በሚሰጥበት አደባባይ
ማለት በዳግም ምጽአት ኃጥአንን
ከጻድቃን ጻድቃንን ከኃጥአን
የሚለይበት ሥልጣን በእጁ ያለ
መሆኑን ያስረዳናል ፤ ስንዴው
ንም በጐተራ ይከታል ገለባውን
ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥላል
የሚለው ቃል የሚአስረዳን ጻድ
ቃንን ከኃጥአን ለይቶ ለዘለዓ
ለም ደስታ መንግሥተ ሰማያት
የሚአገባ ኃጥአንን ከጻድቃን
ለይቶ ለዘለዓለም ሥቃይ በገሃ
ነመ እሳት የሚጥልመሆኑን ነው።

ጻድቃን ከሚአሰኙት ሥራ
ዎች ከዋነኞቹ ጥቂቶቹን ያህል
እንገልጻለን ይኸውም ቅድመ
ዓለም የነበረ መለኮት በኋለኛው
ዘመን ከእመቤታችን ከቅድ
ስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ
ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ሥጋ
ለብሶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ
ሆኖ በተዋሕዶ አምላክ ወሰብእ
መሆኑን ልደቱን፣ ግዝረቱን፣ ጥም
ቀቱን፣ስቅለቱን ሞቱን፣ ቅንግኤ
ውን ፤ ዕርገቱን ዳግም ምዕአ
ቱን አውቆ በማመን በስሙ ተጠ
ምቆ ሕጉን ሥርዓቱን ጠብቆ በጐ
ሥራ ሠርቶየሚኖር ሰው ታላቅ
ጻድቅ ነው ። እንዲህ ያሉትም
ሁሉ ጻድቃን ናቸው።መንግሥተ
ሰማያትም ለእንደዚህ ያሉት
ናቅ ። ኃጥኃን የሚሰኙትም
ደግሞ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን
ባለመፈጸም የሚኖሩ አውቀ
ውም በጎ ሥራ የማይሠሩ ስለሆኑ
ገሃነመ እሳትለእንደነዚህ ያሉት
ናት ። መሆንዋም አይከድም
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትም
ህርቱን ለዓለም ያ ሰ ማ በ ት
በነበረው በ መ ዋ ዕ ለ ቅም
ርቱ ጊዜ «ከውሃና ከመንፈስ ያል
ተወለደ መንግሥተ ሰማያት
ሊገባ አይችልም » ብሎ ያስተ
ማረውና የተናገረው አምላካዊ
ቃሉ የሚያስረዳን በስሙ አም
ነን ተጠምቀን ል ጆ ቹ እንድ
ንሆንና የመንግሥቱ ወራሾች
የክብር ባለቤቶች መሆናችንን
የሚያበሥር ታላቅ የምሥራች
ስለሆነ በፍቅሩ ተስበን በየዓ
መቱ የልደቱን ፤ የግዝረቱን ፤
የጥምቀቱን መታሰቢያ በዓል
ለማክበር ያበቃን አምላክ ክብር
ምስጋና ይግባው ።

ጥበቡ በየነ ፤

## ስለ ሥጋዌ ምን ያውቃሉ ?

በብሉይ ኪዳን ብዙዎች
አበው ቅዱሳን ትንቢትየተናገሩ
ለት ሱባዔ የቈጠሩ ለቅ የመ
ጀመሪያው የሃይማኖት መሠረቅ
ምሥጢረ ሥጋዌ ነበር ፤ ይኸ
ው ም ምሥጢር እግዚአብ
ሔር ለአዳም የሰጠው ተስፋ መበ
ሆኑ ያለማቋረጥ ሲነገር የመጣ
ቢሆንም በመጀ መሪያ አባታችን
አዳም የሰማው የ ተ ስ ፋ ው
ምሥጢርነው ። ይኸው ም ምሥ
ጢር ከሦስቱ አካላት አንዱ
አካል እግዚአብሔር ወልድ ከሰ
ማየ ሰማያት ወርዶ ከአዳምየልጅ
ልጅ መወለዱን ያበሥራል ።

አዳምና ሔዋንከገነት ወጥተው
የብዙ ዘመናት ፍዳ ደርሰባቸው
በፈጸሙት የንስሓ ተጋድሎ የ



www.ethiopianorthodox.org

ይለወጥ ለልጅ ልጅ የሚያልፍ ምሥጢረ እግዚአብሔር በሥጋዌ ተገልጾ በቃል ኪዳን ተሰጣቸው።

ምሥጢር እያሳወቁ የኖሩ የአዳም የልጅ ልጆች ብዙዎች ናቸው እግዚአብሔርም ሥጋዌውን ለመናገር ያበቃቸው ብዙ



የምወደውና የምወልደው ልጄ ይህ ነው እሱንም ስሙት ማቴ ፫—፲፯ ።

ይህንንም ምሥጢረ እግዚአብሔር ሳይቸኩሉ መከራም በመጣባቸው ጊዜ ሳይዘንጉ መከራውንም ሳይሰቀቁ በብዙዎቹ አረማውያንና ከሐድያን አደባባይ እያስተማሩና የሥጋዌውንም

ዎች ቅዱሳን አበው በጾምና በጸሎት በትህርምትና በቀኖና ሆነውበጥትና በግታ በሚያደርጉት ተጋድሏቸው ስለሆነ እግዚአብሔርም ለአዳም በቃል የነገረውን ለልጅ ልጆቹ በራዕይ



ልደት አይተው እስትንፋሳቸውን ገብረውለታል ። ከሰውም ወገን ዮሴፍና ሰሎሜ ከኖሎት ጋር ሆነው አመስግነውታል ። ኋላም ሰብአ ሰገል ሥጋዊውን አምነው ብዙ ዘመናትን አሳልፎ ይኖር የነበረውን የወርቅና የከርቤንም እምኃ አብርክተውለታል ። በልደቱ ጊዜ በሰማይ ብዙ ተአምራት ታይቷል በምድርም የብዙዎች አባቶች ትንቢትና ምሳሌ ተፈጽሟል ። የክርስቶስ ማለት ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በመሆኑ የሚጠራበት ስም ነው ። ኢየሱስም የሥጋዌው ስሙ በመሆኑ በተዋሕዶ አንድ የሆነ አምላክ መድኃኒት ማለት ነው ።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የተዋሕዶ ስሙን ሁሉ ከሥጋዌ ው አግብታ ምእመናንን ታስተምርበታለች የልደቱንም በዓል ሁልጊዜ በዓመት በዓመት ስታ ከብረው ትኖራለች ።

መ| መልአኩ ረለቀ ።

www.ethiopianorthodox.org

# TIMKET (EPIPHANY)

On 19th January (20th January when leap year comes) the Church of Ethiopia celebrates the feast of Timket. This feast, known as Epiphany in most other Churches, is celebrated in commemoration of our Lord's Baptism.

The feast of Epiphany originated in the East, where it was celebrated in remembrance of the Baptism of our Lord and His manifestation to the world, in the third century. From the fourth century Epiphany ranked with Easter and Pentecost as one of the three principal feasts of the Church. It was sometimes celebrated in connexion with the Nativity of our Lord Jesus Christ.

In the Eastern Churches, however, the celebration of the day has the solemn blessing of water as its main feature. This represents the memorial of our Lord's Baptism in the river Jordan, our Baptism as Christians, and also of God's blessing being bestowed on the water as the created element of nature.

The feast of Epiphany was also introduced into the West in the 4th century, but it lost its character as a feast of the Baptism of Christ, which it has retained in the Eastern Church down to the present. Instead, Epiphany became associated in the West with the manifestation of Christ to the Gentiles in the persons of the three Magi. In the West it has been commonly called the feast of the Three Kings of Magi.

In Ethiopia Timket is one of the greatest holy days of the Church, which is celebrated every year as a national holy day. The Church and people observe the feast with warm feeling and ceremonious expressions.

## THE EVE OF TIMKET:

In each part of the country on the eve of Timket a local spring is cleaned and the stream dammed up to make a pool for the ceremony. Clergy and people of all perish Churches in the area make a colourful and joyous procession to the place chosen for the occasion. When they assemble special prayers of the day are said'. People make tents, in which they with priests spend the night in prayer, commemorating the feast.

The eve of Timket is observed as a fast day while Timket itself is a feast day. For this reason the celebration of the mass takes place at midnight.

The eve known as 'Gehad' is associated with the fast days of Christmas and Timket. It literally means revelation and points to the joy and light brought about by Christ's birth. On the eve each church takes part in the procession by bringing ecclesiastical articles required



for the celebration. The faithful of the neighbourhood provide food for priests and others who spend the night in prayer and chanting. They gladly take their turn in this, as the feast is prepared by a different parish church each year. In brief, the whole scene is full of joy; the people participate by dancing and chanting from the time (eve) the ceremony begins and continue till the following day when they return to their respecitve churches.

## TIMKET:

At midnight the liturgical service begins and at dawn the special prayer for the occasion commences. The priests stand around the pool made for the remembrance of Christ's baptism and recite the special prayer for the day blessing the water. When this is done the faithful come and stand around the pool and the priests at the end of the ceremonial prayer sprinkle the holy water on them. If the pool is big enough the people swim in it. This ceremony is not meant to take the place of baptism, but is only a remembrance of Christ's baptism and ours.

During day time on Timket some people, regardless of their age, play Ethiopian hockey. People consider this game a spiritual activity, as they take part in it in fulfilment of vow made during the year that they would thus celebrate Timket. At 12 noon when the ceremony in the place ends, the priests and the faithful make their procession back to their respective Churches.

## WHY WE OBSERVE TIMKET

Although there are many reasons why we celebrate Timket so lavishly, we shall just list the main ones:-

1. We observe Timket in order to commemorate the Baptism of our Saviour Jesus Christ in the river Jordan.

2. We celebrate it to commemorate the day when we Christians were born of God and became children of God through baptism. In other words, we celebrate our own spiritual birthday.

3. We observe Timket because it signifies the manifestation of the mystery of the Holy Trinity - Three Persons in one God - on which our Christian faith is based.

For these and other reasons, Timket has come to be a major festival. On account of the unique character of the celebration of this holy day, tourists from many countries and foreigners living in Ethiopia look forward to seeing the ceremony and the great crowds attending the festival.

## THE RELIGIOUS AND SOCIAL SIGNIFICANCE OF TIMKET

As Timket is a demonstration of Jesus' baptism in action, it is even more effective than preaching as a means



www.ethiopianorthodox.org

of drawing people to the Christian faith. Thus this ancient traditional ceremony is a great attraction for Christians in and outside the country to recall their Christian adherence.

Timket is a festival much looked forward to by the people, as it is a special opportunity for meeting together in public to express their common feelings with joy and folk dancing. For this reason Timket is eagerly awaited and is of cultural and social importance in Ethiopia. Regardless of their socio-economic status people put on new clothes for the occasion. There is even a saying "A dress which will not be worn on Timket should be torn into pieces." This proverb shows that people should wear their best national costumes for the occasion, and even if they have none of their own they should borrow from somebody else. All this makes Timket for Ethiopians a unique symbol of praise to God.

In every christian country Timket is commemorated with special prayers, but not with such elaborate ritual and ceremony as in Ethiopia. Today without any change in the spiritual significance of the feast or alteration of the ancient customs large numbers of tourists come to see the festival. Since Timket in Ethiopia is so unique, people want to know how it began to be celebrated in this way.

Ethiopia received the Gospel and the practice of Christian Baptism very early and the people with their emperors began to celebrate the festival of Timket according to the traditions of the earliest Christian churches. Owing to the Church teaching and owing to the devotion of the people, the ancient customs have been maintained down the centuries without alteration.

Not only Timket but also other celebrations such as the celebration of the finding of the True Cross (Meskel) have also been preserved in a remarkable way in Ethiopia. Thus these two great religious feastivals, Timket and Meskel, are a living testimony to the continuation of the Christian tradition in Ethiopia. They point to the great faith of the people of Ethiopia over the centuries and they are observed every year with great devotion and ceremonious expression.



www.ethiopianorthodox.org